DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of the Chief Operating Officer

ኦክቶበር 17, 2017

ውድ ወላጆች እና ቤተሰቦች፤

የልጅዎ ጤንነት እና ደህንነት በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ለምንገኝ ሁሉ እጅግ ከፍተኛ ግምት የምንሰጠው ነው። የመ ጠጥ ውኃችንን ደህንነት እውን ለማድረግ፣ የጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (DGS) በዲሲፒኤስ (DCPS) ትምህርት ቤቶች ሕንጻዎች ሁሉ የውኃ ደህንነት ማጣሪያ ምርመራ ያካሂዳል። በአለፈው የትምህርት ዓመት፣ የመጠጥ ውሀ ምንጮች በሆኑ ሁሉ አዲስ የውሀ ማጣ ሪያዎች እንዲገጠሙ በማድረግ፣ እነዚህ የመጠጥ ውኃ አገልግሎቶች የእርሳስ (lead) ብከላው ከፍ ባለ ደረጃ መጠን ይገኝ እንደሆነ ለማወቅ ምርመራ ይደረጋል።

በዲስትሪክ ኦፍ ኮሎምቢያ ሕግ መሠረት፣ ለመጠጥ አገልግሎት የሚውሉ የውኃ ምንጮች ሁሉ የምግብ እና የመድኃኔት አገልግሎት አስተዳደር (Food and Drug Administration (FDA)) በጠርሙስ የታሸገ የመጠጥ ውኃን ከሚቆጣጠርበት የጥራት መስፈርት መጠን መለኪያ መሠረት ከ 5 ppb (parts per billion) (ከቢሊዮን ውስጥ 5 እጅ) በታች ዝቅ ብሎ የሚገኝ መሆን ይኖርበታል።

ለ 2017-2018 የትምህርት ዓመት የውኃ ማጣሪያ ፊልተሮች ሁሉ የሚለወጡ ሲሆን፣ የጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (DGS) የእር ሳሱ መጠን (lead) ከፍ ብሎ ስለመገኘቱ ሁኔታ የማጣሪያ ምርመራ ያካሂዳል። ምርመራው ስለሚካሄድባቸው ስለ ልጅዎ ትምህርት ቤት የተወሰኑ የምርመራ ማጣሪያ ቀናት ለማወቅ እባክዎ https://dcps.dc.gov/page/water-testing-lead.ን ይቃኙ።

**በምርመራው መሠረት በመጠጥ ውኃው ውስጥ የሚገኘው መጠን ከ 5 ppb የሚበልጥ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ** ስለ ምርመራው ውጤት ለወላጆች እስከምንገልጽበት ጊዜ ድረስ እና ችግሩንም ለማቃናት የጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (DGS) ምን እያ ደረገ እንደሆነ እስከሚያስታውቅበት ድረስ፣ የውኃ ቧንቧዎቹ አገልግሎት ወዲያውኑ እንዲቋረጥ ይደረጋል። በዲስትሪክቱ የውኃ ማጣሪያ እና የምርመራ ደንብ ሥነ ሥርዓት መሠረት፣ የመፍትሄ ሀሳቦች፣ የየቧንቧዎቹ (faucets) ማጣሪያዎችን ፣ የመገጣጠሚያ መገናኛዎችን፣ እና በአንዳንድ ሁኔታዎችም ልዩ ልዩ የውኃ ቧንቧዎች በሌሎች ሁኔታዎችም የቧንቧ ክፍሎችን በአዲስ መቀየርን ይጠይቃል። **ለመጠጥ የሚውል የውኃ ምንጭ፣ በድጋሚ እስከሚመረመር እና ውጤቱም ከ 5 ppb በታች ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ አገልግሎት እናዲሰጥ አይደረግም።**

ለመጠጥነት የማይውሉ የውኃ ባንቧዎች፣ ለምሳሌ የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የመሥሪያ ክፍሎች (utility closets) እጅ ለመታጠቢያነት ብቻ ደህንነት ያላቸው ናቸው። እንደነዚህ ያሉ የመታጠቢያ እና የመጸዳጃ አገልግሎቶች ለመጠጥ ውኃነት አገልግሎት እንዳይውሉ ለተማሪዎች ለማስገንዘብ በግልጽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያዎች እንዲለጠፍባቸው የተደረጉ ናቸው።

ስለ እርሳስ (lead) የበለጠ ለመረዳት፣ በትምህርት ቤትም የውኃ ደህንነት ብሄራዊ መስፈርት (national standards) ጉዳይ ለማወቅ እና ስለምርመራ አከናወን እርምጃዎች ሥርዓት ሁኔታዎች ለማንበብ እባክዎን በሚከተሉት ድረ ገጾች ይጠቀሙ።

- http://doee.dc.gov/lead
- https://www.epa.gov/dwreginfo/lead-drinking-water-schools-and-child-care-facilities
- https://dgs.dc.gov/publication/water-filtration-testing-protocol

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን (202) 442-5192 ይደውሉ ወይንም በ schooloperations.dcps@dc.gov. ኢሜይል መልእክት ይላኩ። ቀጣይነት ላለው ድጋፍዎ እናመሰግናለን።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Carla Watson
ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
(Chief Operating Officer, DC Public Schools)